
# የአዲስ አበባ ብልጽግና ፓርቲ ጽ/ቤት

## የገዥ ትርክት ግንባታ

## (ለብልጽግና ፓርት አባላት የቀረበ መወያያ ጽሁፍ)

ታህሳስ/ 2016 ዓ.ም
አዲስ አበባ

# የውይይቱ ይዘት



መግቢያ
አብሮነት፣ሥነ ምግባር እና ትርክት
ትርክት፣ተረክ እና ታሪክ
ከብሔርተኝነት ወደ ብሔራዊነት የብልጽግና ገዢ ትርክት
ብሔራዊ ትርክትን ለማስረጽ የምንጠቀማቸው መንገዶች
በአርበኝነት የሚፈጠር ብሔራዊነት ገዢ ትርክት እንዲሆን የአመራሩና የአባላት ሚና
ማጠቃለያ.

# 1. መግቢያ

ፓርቲያችን በአንድ በኩል ጠንካራ ሀገር የመገንባት፣ በሌላ በኩል ደግሞ የሀገራችን ሕዝቦች ሕይወት የሚለወጥ ዕሴት መፍጠርን ያነገበ ነው፡፡.


ያልተለወጠ የፖለቲካ ባህላችን ዕሴት ለማፍራት እንዳንች ፈተና በመሆን ከዕዳ ተሸግረን ወደ ምንዳዕ መንደርደር እዳንችል አድርጎናል፡፡

እንደ ሀገር ለዘመናት የቆየ አካሄዳችን ከዕዳ ወደ ሌላ ዕዳ የሚወስድ ተመሳሳይነት ያለው አዙሪት ነው፡፡

ፓርቲያችን ብልጽግና ባለፋት የለውጥ ዓመታት በፖለቲካ ባህላችን ውስጥ ለውጥ ማምጣት የሚስችል አዲስ የፖለቲካ አካሄድን ተከትሏል፡፡

# መግቢያ… የቀጠለ

አሁን ላይ ሀገራዊ ዕዳን ቀን ሰው ምንዳዕን የሚበዙልን ***ሁለት ቁልፍ*** ወቅታዊ አጀንዳዎች ከፊታችን ቆመዋል።



1. የመጀመሪው ሕዝብን አስተባብሮ የጋራ ዓላማን የሚፈጥር ሀገራዊ ገዢ ትርክት መፍጠር ሲሆን፣
2. ሁለተኛው ይህንን ዓላማ ለማስፈፀም የሚስችል ሥነ ሥርዓት ነው።

በመሆኑም ባሳለፍናቸው በጀት ዓመታት የሠራናቸውን ሀገራዊ ዕዳን የሚቀንሱ ድሎችን በማጠናከር፣ በአዲሱ የበጀት ዓት ጉድለቶቻችን በማረም፣ ድሎቻችን በማስቀጠል፣ ለዘመናት የተከማቹ ሀገራዊ ዕዳዎችን በማራገፍ፣ ወቅቱ የሚፈልገውን ሁለተኛውን የዐርበኝነት ምዕራፍ ማስጀመር አለብን።

# 2. አብሮነት፣ሥነ ምግባር እና ትርክት


አብሮነት፣ሥነ ምግባር እና ትርክት

1. እኛ ኢትዮጵያዊያን የተሣሠረ ህልውና እና የተጋመደ ማንነት ባለቤት ነን
2. የውል ትርክት አገር ያድናል፤ የተሳሳተ ትርክት አገር ያጠፋል
3. ትርክት ምንድ ነው?
4. ገዥ ትርክት ለምን ይጠቅማል?

# 2.1. እኛ ኢትዮጵያዊያን የተሣሠረ ህልውና እና የተጋመደ ማንነት ባለቤት ነን

አብሮነት ከግለሰቦች እስከ ሀገራት ድረስ በተሸለ ሁኔታ ህልውናን የማስጠበቂያ መንገድ ነው::

የሰው ልጅ በተናጠል ህልውናውን የማስጠበቅ ክፍተት አለበት::



ህልውናውን ማስጠበቅ እና ወደ ዕድገት ማምራት የሚችለው ከሌላው ጋር በመደመር ነው::


አውሮፖውያን ይህ ስለገባቸው በውስጣቸው ካለው አንድነት ተሻግረው አህጉራዊ ኅብረታቸውን ለማጠናከር ይሠራሉ::

# የቀጠለ.. .የተጋመደ ማንነት ባለቤት ነን

የአንዳችን ህልውና በሌሎቻችን ላይ ጥገኛ ስለሆነ የራሳችንን ደህንነት ለማስጠበቅ የሌሎችን ደህንነት መጠበቅ አለብን፡፡

አማራ ደኅና ሳይሆን ደኅንነቱ የሚጠበቅ ኦሮሞ፣ ኦሮሞ ደኅና ሳይሆን ደህንነቱ የሚጠበቅ ሱማሌ የለም፡፡ አንዱ ደህና ሳይሆን ሌሎቻችን ደህና አንሆንም፡፡ የሁላችንም ዕጣ ፋንታ በጋራ ደህንነታችን ላይ ይመሰረታል፡፡

አብሮነት በአንድ በኩል መሰባሰብና መቀራረብን በመፍጠር እርስ በእርስ የሚኖር ሽኩቻን ይቀንሳል፡፡ በሌላ በኩል አብሮነት በተሻለ መልኩ ችግሮችን እና ፈተናዎችን ለመቋቋም እንዲሁም ከፍ ያሉ ውጤቶችን ለማስመዝገብ እድል ይሰጣል፡፡



# 2.2. የውል ትርክት አገር ያድናል፤ የተሳሳተ ትርክት አገር ያጠፋል

ትርክት የአብሮነት ታሪካዊ መሰረት ነው::

ለአብሮነታቸው ትርጓሜ የሚያገኙት ከትርክት ነው::

.



ሰዎችን ከየት እንደተነሡ እና ወዴት እንደሚደርሱ የሚያመለክታቸው ትርክት ነው::

ትርክት የወደፊ ተስፋን እና ዛሬ ላይ የሚኖረውን ሚና የሚከሰቱ ክስተቶችን የምንመለከትበት መነጽር ነው::


# 2.3. ትርክት ምንድ ነው?

ትርክት ማለት (የወል ወይም የጋራ) የሚለው ቃል የአንድን ማኅበረሰብ ወይም ሕዝብ የወል ማንነት ለመግለጽ የሚያገለግሉ፣ በቅደም ተከተል የተሰነዱ እና በማህበረሰቡ ባህልና ምግባር በሰፊው ተቀባይነት ያገኙ ታሪካዊ እና ነባራዊ ክሥተቶች፣ ቁሳዊና ኢ-ቁሳዊ ትሩፋቶች እና ዕሴቶች ማለት ነው::

ትርክቶች ታሪካዊ ክስተቶችን ፣ባህላዊ፣ ኢኮኖሚያዊና የፖለቲካ ተሞክሮዎችን ተንተርሰው ከአንድ ትውልድ ወደ ሌላ ትውልድ በሀገር እና በማንነት ግንባታ ሂደት ፣በተለያዩ የማህበራዊነት ወኪሎች ( ትምህርት፣ ማህበረሰብ ፣ መገናኛ ብዙሀን (ሚዲያ) ቤተሰብ፣ ፖለቲካ ድርጅቶች እና ሌሎች አካላት መካከል ይተላለፋል::

# 2.4. ገዥ ትርክት ለምን ይጠቅማል?

ትርክት ግለሰቦችም ይሁን የተለያዩ የወል ማንነቶች የጋራ ዓላማና ታሪካዊ ዳራ እንዲኖራቸው ያግዛል::





ትርክት አስተሳሰብን እና እውነትን በተመለከተ ያለንን አመለካከት ቅርጽ ያስይዛል

ትርክት የባለፈውን ጊዜ የምንረዳበትና ክሥተቱን የምናስታውስበት ብቻ ሳይሆንስለ አንድ ሕዝብ በሚኖራቸው አረዳድ፣ አመለካከትና ተግባር ላይ ተጽዕኖ ያሳድራል::

ትርክት በውሳኔዎችም ላይ ተጽዕኖ ያሳድራሉ::

በአጠቃላይ ገዥ ትርክት አንድነቷ የተጠበቀች አገር ለገንባትና የነገ አገር ተረካቢ ትውልድ ለማነጽ በእጅጉ ያስፈልጋል::

# 3. ትርክት፣ ተረክ እና ታሪክ




በሰው ልጆች ታሪክ ውስጥ በእውነት ስለተደረጉ ነገሮች በማስረጃና በመረጃ ተመሳክሮ፣ በጊዜ ቅደም ተከተል መሰረት የሚቀርብ ታረካ ነው፣ በአጠቃላይ ታሪክ ከየትና እንዴት እንደመጣን የሚገልጽልን የትናንት ትረካ ብቻ ሳይሆን የዛሬውን ለመረዳት የሚያግዘን የትምህርት ገበታ ነው፡፡


ተረክ /Story/ ግን ስለ አንድ ታሪክ፣ ገጠመኝ፣ ኩነት፣ ድርጊት ሃሳብ የሚነገር ፈጠራ የታከለበት ትረካ ነው፡፡

ትርክት ማለት (የወል ወይም የጋራ) የሚለው ቃል የአንድን ማኅበረሰብ ወይም ሕዝብ የወል ማንነት ለመግለጽ የሚያገለግሉ፣


# 4.  ብሔርተኝነት ወደ ብሔራዊነት የብልጽግና ገዢ ትርክት



ብሔርተኝነት




“ብሔራዊነት” የብልጽግና ገዥ ትርክት



ገዥ ትርክታችንን እንዴት መገንባት ይቻላል?

# 4.1. ብሔርተኝነት



1

- ብሔርተኝነት ማለት አንድን ተፈጥሯዊ፣ ማህበራዊ፣ አካባቢያዊ፣ ፖለቲካዊ ወይም ኃይማኖታዊ ማንነትን መሰረት አድርጎ የሚቀነቀን ርዕዮት ዓለም ነው፡፡
- መሪ ሐሳቡ የአንድ ግለሰብ ታማኝነት ከሁሉ ዓይነት የግል ወይንም የቡድን ፍላጎት በላይ ለብሔሩ ወይንም ለብሔረ መንግስቱ ነው የሚል ነው፡፡

2


- ብሔርተኝነት የብሔርን ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና በተለይ ደግሞ ምጣኔ ሀብታዊ ጥቅም ለማሳደግ የሚጥር ሥርዓት ነው፡፡
- ብሔርተኝነት አንድ ብሔር ከተጋረጠበት የህልውና አደጋ ራሱን ለማዳን የሚጠቀምበት የፖለቲካ ርዕዮት ዓለም ነው፡፡

3

- በዓለም ላይ ከአሥር አራት ዓይነት በላይ ብሔርተኝነት እንዳለ መረጃዎች ያሳያሉ ይህም የባህል፣ የብሔረሰባዊ፣ የሲቪክ፣ የሊብራል፣ የሃይማኖት፣ የግራ ዘመም እና የኢኮኖሚ ብሔርተኝነት በዋነኝነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

# 4.2. “ብሔራዊነት” የብልጽግና ገዥ ትርክት

“ብሔራዊነት” ማለት “ሕገ-መንግስታዊነትን መሰረት ያደረገ ኅብረ-ብሔራዊ አንድነት” ማለት ነው::



” ሕገ-ምግስታዊነት ” ማለት ህዝቦች ተስማምተውና ተግባብተው በሕገ መንግስታቸው ላይ ባስቀመጧቸው እሴቶች መሰረት ሀገረ-መንግስት ለመገንባት መቻል ነው::

# የቀጠለ .... ብልጽግና ብሔራዊነት ገዥ ትርክቱ እዲሆን ለምን ፈገለ?

ብልጽግና አማካይ እሳቤን የሚያራምድ መሆኑ

ብልጽግና በጋራ ነገሮቻችን ላይ ስለሚያተኩር

ብሔራዊነት ከዋልታ ረገጥነት የወጣ ነው።

ብሔራዊነት ሀገራዊ መግባባትን ዕውን ያደርጋል

ብሔራዊነት ለሁሉም እኩል ዕድል ይሰጣል

## 4.2.1. ብልጽግና አማካይ እሳቤን የሚያራምድ መሆኑ

ፓርቲያችን ኅብረ ብሔራዊነትን፣ አካታችነትን፣ ፍትሐዊነትን እና እኩልነትን ለሁሉም ኢትዮጵያውያን የሚያረጋግጥ አሳባሳቢ ትርክ ሀገራችን ያስፈልጋታል ብሎ ያምናል።

አብሮነትን ክዶ ልዩነት ላይ ብቻ የሚተኩር ትርክት፣ ብዝኃነትንም ደፍጥጦ ፍጹማዊ አንድነት ላይ ቅድሚያ የሚሰጥ ትርክት ለምናስበው ሀገራዊ ሁለንተናዊ ብልጽግና አይጠቅመንም።

# 4.2.2. ብልጽግና በጋራ ነገሮቻችን ላይ ስለሚያተኩር

ብሔራዊነት የህዝቦችን የጋራ ጉዳይ ማጉላት ነው፣

በአንድ ሀገር ውስጥ የኖርን፣ ለአንድ ሀገር እኩል ዋጋ የከፈልን፣ በዚህች ሀገር የመጡ ዕድሎችንና መከራዎችን እኩል የተጋራን፣ አንድነታችንም ማንነታችንን የማይጠፋብን፣ዛሬን አጥብቀን የምንሰራ፣ ነገን በርትተን የምንገነባ ሕዝቦች ነን ብሎ በፅኑ ያምናል፡፡

# 4.2.3. ብሔራዊነት ለሁሉም እኩል ዕድል ይሰጣል

4. ብሔራዊነት በኢትዮጵውያን ላብ እና ደም ድምር ጥረት የተገነባች፤ በድምር ጥረቶቻቸው የምትበለጽግ ሀገር ናት ብሎ ማሰብ ነው


3. ብሔራዊነት በአንድነት የሚፀና ብዝኃነት ነው፤ በብዝኃነት የሚዋብ አንድነት ነው

2. ኢትዮጵያውያን ቋንቋ፣ ባህል፣ ራስን በራስ ማስተዳደር እና ሌሎችም ፍላጎቶች እኩል ዕውቅና ይሰጣል፤ ሁሉም ኢትዮጵያዊያን በሀገር ጉዳይ ላይ እኩል ተሳትፎና ተጠቃሚነት እንዲኖራቸው የሚያስችል እሳቤ ነው::

1. ብሔራዊነት ይሄኛው ማንነት በተለየ ሁኔታ ሊደገፍ የሚገባ ነው አይልም::


# 4.2.4. ብሔራዊነት ሀገራዊ መግባባትን ዕውን ያደርጋል

ብሔራዊነት ችግሮችን እየሸፋፈኑ መሰረት አልባ የሆ ሀገራዊ አንድነት መትከል እይደለም፡፡




ብሔራዊነት በገዢ ትርክቶች ማዕከላዊ ዕሳቤ ላይ ለመግባባት የልዩነት ምንጭ የሆኑ መሰረታዊ ችግሮች ላይ በመነጋገር፣ በመደራደርና በመወያየት መፍታት ነው፡፡

# 4.2.5. ብሔራዊነት ከዋልታ ረገጥነት የወጣ ነው።



# 4.3 ገዥ ትርክታችንን እንዴት መገንባት ይቻላል?




## 4.3.1. ገዥ ትርክትን በአስተሳሳሪ ትላንት ላይ መገንባት

ገዢ ትርክታችን የሆነው ብሔራዊነት፣ አስተሳሳሪ ትናንቶች እና አስተሳሳሪ ነገሮቻችን የሚፀኑበት ትርክት ነው።

ሕዝባችን ብዙ አስተሳሳሪ ትናንቶች አሉት በየወቅቱ በውስጣዊ አንድነት ብንፈተንም ሀገራዊ ህልውናችንን ሊፈታተን የሚመጣን ጠላት አሳፍሮ የመመለስ አኩሪ ታሪክ አለን።

ግብጽን ከጉንዴት እስከ ጉራ፣ ደርቡሽን በመተማ፣ ጣልያንን በአድዋ፣ የዚያድ ባሬዋን ሶማልያ ድል አድርገን ሀገራዊ እንድነታችንን አስጠብቀናል።



## 4.3.2 ገዥ ትርክትን በአስተሳሳሪ ነገ ላይ መገንባት

ከራዕይ ወደ ተግባር እየተቀየረ ያለውን ሕልማችንን በሦስት መዳረሻ ምዕራፎች በመከፋፈል እየሠራን እንገኛለን፡፡ እነሱም


01 በራዕይ 2018 ኢትዮጵያን “ከተስፋ ብርሃን ወደ ሚጨበት ብርሃን” መሸጋገር

02 ራዕይ 2013 ኢትዮጵያን “ የአፍሪካ የብልጽግና ተምሳሌት” ማድረግ

03 ራዕይ 2040 ኢትዮጵያን “ ዓለም አቀፍ የብልጽግና አርአያ ” እንድትሆን ማስቻል ናቸው፡፡

## 4.3.3 ዐርበኝነትን ለብሔራዊነት በመጠቀም

ዐርበኝነት የሀገርንና የወገንን ደህንነትና ክብ በተመለከተ ከቶ የማይደራደሩበት በእውነተኛ ሕዝባዊ ፍቅር ላይ የቆመ ሰብእና ነው፡፡





በመሆኑም ዐርበኝነት ስንል ለሀገር እና ለሕዝብ ታማኝነት (Loyalty)፣ ሀገርንና ሕዝብን መውደድ Love)፣ ለሀገርና ለሕዝብ መቅናት (Zeal)፣ መስጠት (DevotioN), መጣበቅ (Attachment)፣ ድጋፍና ተከላካይነት Support and safeguard ማለት ነው፡፡

ዐርበኝነት ለሃገር ክብር፣ ሉዓላዊነት፣ ነፃነት ፣ እድገትና ብልጽግና ሲሉ ላቅ ያለ መስዋዕትነት መክፈል ነው፡፡

# የቀጠለ….አርበኝነት በኢትዮጵያ ሁለት ምዕራፎች አሉት እነርሱም

ተዋጊ አርበኝነት፡-
የመጀመሪያው ምዕራፍ ሀገርን ከውጭ ወራሪ በመካከል ሉዓላዊነቷን ማስከበር እና ነፃነቷን ማስጠበቅ ነው፡፡



የብሔራዊነት ዐርበኝነት፡- ይህ ሁለተኛው እና ረጅሙ የዐርበኝነት ምዕፋፍ ውስታዊ ልዩነቶችን በማጥበብ የህዝቦች እኩልነት፣ ፍትሐዊነት እና ያለንበት ወቅት ይህ የዐርበኝነት ምዕራፍ በፓርቲያችን ድል አድራጊነት የሚጠናቀቅበት ምእራፍ ነው፡፡

## 4.3.4 የብሔራዊነት ዐርበኝነት አዕማድ የሚባሉትን ከልብ በማመንና በመተግበር




ብዝኃነት፡-.

አብሮነት፡-

ፍትሐዊነት፡-.

እኩልነት

## 4.3.5 አዳዲስ አፍራሽ ትርክቶችን በመገዳደር

ፓርቲያችን ውርስ ችግሮቻችንን ለመፍታት አራት መንገዶችን ይዞ እየሰራ ነው፡፡

**01**

ሪፎርም፡- የቀደሙ ኢኮኖሚያዊ፣ ሕጋዊና መዋቅራዊ ችግሮችን ለመፍታት ሪፎርም አዘጋጅተን እየሰራን ነው፡፡ በዚህ ሪፎርም ሕግጋትን አሻሽለናል፣ መዋቅሮችን ቀይረናል፡፡

**02**

የትርክት ለውጥ፡- ከፍጹማዊ አንድነት እና ከልዩነት ትርከቶች በመውጣት ሁላችንንም ሊያሰባስብ፣ ጉድለቶችን ሊሞላና ስህተቶችን ሊያርም የሚችል አዲስ ትርክት እያዘጋጀን ነው፡፡

**03**

የሽግግር ፍትሕ፡- በዘመናት የተፈጠሩ የሕግ ጥሰቶችን ለማረምና መኅበራዊ ርካታ ለመፍጠር የሽግር ፍትሕን መንገድ እየተከተልን ነው፡፡

**04**

ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽን፡- የቀደሙ ሀገራዊ ችግሮቻችንን ለመፍታትና ሀገራዊ ተግባቦትን በዋና ዋና ጉዳዮች ላይ ለማምጣት የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ተቋቁሞ ሥራ እየሰራ ነው፡፡

## 4.3.6. የተናጠል ትርክቶችን በመገዳደር

በሀገራት የተለያዩ ምልከታዎችን ተከትሎ የሚከሰቱ አለመረጋጋቶች ለሀገር መንግስታችን ትልቅ ፈተናዎች ናቸው፡፡

የሂሳብ ልዩነትን ተከትሎ የሚቀርጹ ትርክቶች ለአብሮነት ሳንካ ናቸው፡፡

ትርክቶች የሐሳብ ልዩነትን የሚመለከቱበት መንገድ እየተለያዩ ሀሳቦችን ለማስተናገድ የሚመርጡት አካሄድ ለውጥን ለማምጣት በሚደረገው ጥረት ላይ ከፍተኛ መሰናክል የሚጥል ነው፡፡

# 4.3.7. ሕዝበኝነትን በጽናት በመዋጋት




በሤራ ትንታኔ የታጀለ ትርክት የሚያቀነቅን ልሂቃን ግለሰባዊ ወይም ቡድናዊ የሆነ ነፍላጎቶቻቸውን ለማሳካት የሚጠቀሙበት ዋነኛው መንገድ "ሕዝቡ" የሚለውን መፈክር ነው።

ትንታኔዎቻቸው "ሕዝቡ እዲህ ነው" "ሕዝቡ የሚፈልገው ይሄንን ነው" ሕዝቡ ተቆጥቷል፣ ሕዝቡ ጠየቀ የሞሉ በሕዝቡ ስም መኃላ የሚበዛባቸው ናቸው።

"ሕዝቡ" በሚል ትልቅ ጃንጥላ ሥር የሚያስፈጽሙት የራሳቸውን ፍላጎት ነው።

## 4.3.8. የጥላቻ ፕሮፖጋንዳ እና የሤራ ትንታኔን መዋጋት

የጥላቻ እና የሤራ ትንታኔ ግቡ መለያየትን እና የአንድ ወገን የበላይነትን መፍጠር ነው፡፡ ስለዚህም ሥነ ምግባራዊ መነሻና መሰረት የለውም፡፡

አብሮነትን በመናድ የአንድ ወገንን አልያም የግልን ጥቅም ማሳካት የሚሻ በመሆኑ ከይቅርታ፣ ከመተማመን እና ከመቻቻል ይልቅ ፍርሃትን፣ ጥላቻን፣ ጥርጣሬን እና አለመግባባትን የሚመርጥ ነው፡፡

# 4.3.9. ኃይል እና ዐመጽ መንገዶችን በመዋጋት

የሜራ ፖለቲከኞች ትርክቶች መሬት ላይ በዐመጽና በትጥቅ እንቅስቃሴ የታገዙ ናቸው።

ትርክቶቹ የተወሰኑ ወገኖችን በስሜታዊነት መቀስቀስ ቢችሉም፣የተወሰነ አደጋ በማድረስ ነውጥ ቢፈጥሩም፣ የብዙኃኑን ወገን ተቀባይነት አግኝተው ገዥ መሆን አይችሉም።

በሀሳብ መራመድ ያልቻሉትን በትጥቅ ሊራመዱት ይነሳሉ። ዐመጽን እና የትጥቅ እንቅስቃሴን እንደ ፍላጎት ማስፈፀሚያ መንገድ ይጠቀሙበት።

# 5. ብሔራዊ ትርክትን ለማስረጽ የምንጠቀማቸው መንገዶች

5.1.
በስትራቴጂ
የሚመራ የሚዲያ
አካሄድን በጥብቅ
ዲሲፕሊን
ተግባራዊ
ማድረግ፤

5.2.
ተግባራዊ
ተምሳሌታዊነት
ን ሥራ ላይ
ማዋል፤


5.3.
ትምህርት ዋነኛ
የትውልድ
ልማት
መገንቢያ
አድርጎ
መስራት፤

.

# 5.1. በስትራቴጂ የሚመራ የሚዲያ አካሂድን በጥብቅ ዲሲፕሊን ተግባራዊ ማድረግ

በኮሚኒኬሽን መዋቅራችን፣ በየደረጃው የሚገኙ በሺዎች የሚቆጠሩ የኮሙኒኬሽን ኃላፊዎችና ባለሞያዎች ዋነኛ አላማቸው የብሔራዊነት ትርክትን መገንባት ነው ፡፡

የመንግት የሥራ ኃላፊዎች፣- አመራሮች/ ዋነኞቹ የመንግስት የኮሙኒኬሽን መንገዶ ናቸው፡፡



የፓርቲና የመንግስት መድረኮች፣- የብሔራዊነትን ትርክት የሚገነቡ መሆን አለባቸ

የመንግስት ሚዲያዎች፣- ዜናዎችን ከመዘገብ እና እውነትን ከማጋለጥ በላይ ዋነኛ ሚናቸው የትርክት እና የትውልድ ግንባታ መሆን አለበት፡፡

# 6. ዐርበኝነት የሚፈጠር ብሔራዊነት ገዢ ትርክት እንዲሆን የአመራሩና አባላት ሚና

**1**

**መታመን፡-** ታማኝነት የሐቀኛ አርበኝነት ቀዳሚ መርሕ ነው

**2**

**መስጠት፡-** ለዓላማው የታመነ አርበኛ ለታመነበት አላማ መስጠትን ይላበሳል።
የፓርቲያችን አመራርና አባል የወቅቱ የአርበኝነት መርህ መስጠት ነው።

**3**

**መጠበቅ፡-** ሀገራችንን ከስሑት ትርክት መጠበቅ የ የአርበኛ አመራር እና አባል ዋነኛው መርህ ነው። በልዩነት ላይ ከተመሰረተ ከፋፋይ ትርክትና ፍፁማዊ አንድነትን ይዞ ወጥ ማንነትን ለመገንባት ከሚመጣው ፍፁማዊ ትርክት መጠበቅ ዋነኛው መርህ ሊሆን ይገባል።



# ማጠቃለያ

**ፓርቲያችን ብልጽግና፣-**

- ከሀገራችን ፖለቲካዊ ስራብቶች ከወረሳቸው ውርስ የቤት ሥራዎቹ ውስጥ ዋነኛው ገዢ ሀገራዊ ትርክት አለመገንባቱ ነው፡፡
- ገዢ ሀገራዊ ትርክታቸው ዘላቂ የሀገር መርሕ ሆኖ ሀገር እንዲያጸና ያደርጋሉ፡፡ በሀገራችን የተራራቁ ትርክቶች ካለፉት ሃምሳ ዓመታት ጀምሮ የፖለቲካ ገበያውን ተቆጣጥሮታል ፡፡

**የብሔራዊነት ዐርበኝነት፣ ነጠላ እና አግላይ አይደለም፣-**

- አስተሳሳሪ እና አካታች ዐርበኝነት ነው፡፡
- ኢትዮጵውያን የሀገርን ነፃነት የማስጠበቅን ወረት ይይዛል፡፡
- የነገሠውን የነጠላ ብሔር አቀንቃኝነት (የልዩነት እና የአንድነት ትርክት አቀንቃኞች) ያከስማል፣ በጋራ አስተሳሳሪ ትርክት እና ለጋራ ነጋችን ለሆነው ሁለንተናዊ ብልጽግና መሰረት የሚሆን የብሔራዊነት ዐርበኝነትን በአብሮነት ያቆማል፡፡

# አመሰግናለሁ!!